# ምክረ-ሃሳብ ለሀገር ግንባታ

**ብስራት ኢብሳ (ሆላንድ)** **1-6-2019**

ይህንን አስተያየት ለመጻፍ ያነሳሳኝ ምክንያት **“በኢትዮጵያ የተሳካ የሀገር ግንባታ እውን ለማድረግ”** በሚል ርዕስ ሀገር ውስጥ የተጀምመረና፣ በአውሮፓም ትኩረት አግኝቶ ዜጎቻችንን እያወያየ ካለ የመመካከርያ መድረክ የተላለፈውን ዘገባ ካነበብኩኝ ቦኋላ ነው፡፡ ይህ በዋልታ የተላለፈው 4 ተከታታይ የውይይቱን ፊድዮዎች በዩቲዩብ አግኝቼ ስከታተል በውስጤ አሳዛኝም ሆነ አስገራሚ ስሜት አስተናግጃለሁ፡፡

ወቅቱ ከአንድ ሁለት ዓመት በፊት የለውጥ እንቅስቃሴው ግፊት ጣራ በደረሰበት የመጨረሻዋ የምጥ ሰዓት፣ ለውጡን ለማዋለድ ይሁን ለተገላቢጦሽ እርግጠኛ አይደለሁም፣ ይህ ጠቃሚ ሲምፖዚየም ሲጀመር፣ ከፍተኛ የሀገሪቷ ባለስልጣኖችና በርካታ የመስኩ ምሁራኖች፣ ታዋቂ የታሪክ ተመራማሪዎች፣ የብሔርና የዜግነት ፖለቲካ የሚያራምዱ መሪዎችና ታዋቂ ግለሰቦችን ያካተተ ነበር፡፡ ባጭሩ በሀገር ጉዳይ ማንም ያለውን ችግር አስተውሎና ተነሳሽነቱን ወስዶ፣ ለችግሩ መፍትሄ በመሻት ሌሎችንም ሰፋ ባለ መንገድ አካቶና የጋራ አጀንዳ ቀርፆ መላ መፈለግ ሊበረታታና ሊያድግ የሚገባው አካሄድ ነው፡፡

ምናልባት ይህ ተነሳሽነት በከፊል የተለወጠው የኢሕአዴግ አስተዳደር፣ በወቅቱ ይካሄድ በነበረው ውስጣዊ ትግልም ይሁን ከውጭ የሕዝባዊ ግፊት ጫና፣ ነገሮችን ለማስተንፈስም ይሁን በሕዝባዊ ተሳትፎ ስም እየመጣ የነበረውን ጎርፍ አቅጣጫውን በራሳቸው መንገድ ቀይሰው ሕጋዊ መሠረት ለማስጨበጥ የጀመሩት ዕቅድ እንኳን ቢሆን? ችግሩ እንዲያውም በባሰ ሁኔታ ተወሳስቦ እየቀጠለ ስለሆነ፣ የመፍትሄ ማፈላለጉ ተነሳሽነት አሁንም ሆነ ወደፊትም ለበረታታ ይገባዋል፡፡

ባለፈው አንድ ዓመት ጥቂት የማይባሉ ብዙ ተስፋ ሰጥተውን የነበሩ አበረታች እርምጃዎችን እንዳደነቅን ሁሉ፣ በአንጻሩ አሁን ደግሞ ብዙ ነገሮች ወደ አልተፈለገ መስመር አቅጣጫቸውን እየቀየሩ መጪውን ጊዜ ጥላ ሲያጠላበት እናያለን፡፡ እንደ ሀገር እንዳንቀጥል እንቅፋት የሆኑብን ዋና ዋና የሆኑት ችግሮች፣ ሕገ-መንግስታዊ መሠረትና የአዋጅ ሽፋን አግኝተው አደጋ ላይ እየጣለ ያለ እውነታ እንዳለ ሆኖ፣ በነበሩት ችግሮች ላይ አዳዲስ ታክለውበታል፡፡

ባጠቃላይ በምሁራኑ የቀረቡት ታሪኮቻችን፣ ከተሳታፊዎች የተነሱት ጥያቄና መልሶች፣ አስተያየቶች፣ ጠቃሚና ትምህርታዊነታቸው የማያጠያይቅ አይደለም፡፡ በአንጻሩ በዕድሜያችን የምናውቃቸውን ግልጽ እውነታዎች፣ በሰነድና በሕይወት ያሉ ምስክሮች ሊያረጋግጡ የሚችሉትን ታሪኮች፣ በአንዳንድ ተሳታፊዎች ሲካዱና ሲበረዙ ተሰምቷል፡፡ ለአንዳንዶቹ ዛሬ የምናየው ችግር እንዴት? ለምን? በማን የሚለውን በለሆሳሳ አልፈውት፣ ባለፈው ላይ ብቻ ትኩረት ሲሰጡ፣ ሌሎቹ በተለያዩ ሀገሮች በሃይል ጭምር የተካሄዱትን የሀገር ግንባታ በኛ ከተካሄደው ጋር እያዛመዱ እውቀታቸውን ሲያካፍሉን፣ ጥቂቶች ዛሬ ያለውን ችግርና ነገ ምን አይነት ሀገር እንድትሆንልን እንፈልጋለን የሚለውን በዘመናዊ የቴክኒዮሎጂ እርዳታ በስዕላዊ ገለጻና በምሁራዊ አገላለጽ የሚችሉትን አድርገዋል፡፡

ይህ ሁሉ ሆኖም፣ እንደ ተራ ዜጋ የምናያቸው፣ በተለያየ የመገናኛ መዋቅር የምንሰማቸው፣ በየስፍራው በተጨባጭ እየተፈጠሩ ባሉ እንደ ሀገር እንዳንቀጥል የሚያስችሉ ችግሮች ዙርያ በውይይቱ በቂ ትኩረት ያላገኙትን አውጥቶ በመጠቆም፣ ለመፍትሄው ትንሽ ጠብታ ያህልም አስተዋጾ ማድረግ፣ የወቅቱ አጣዳፊ ተግባርና የሁሉም ዜጋ ሃላፊነት ነው፡፡

ከዋናው አርስቴ ላለመውጣት በዚህ ውይይት ከታዘብኳቸው አስተያየቶች ሁለቱን ብቻ አካፍላለሁ፡፡

ትዝብት አንድ፣ ኢሕአፓና ወያኔ “በኤርትራ የኮሎኒ ጥያቄ” ድሮ ወስደውት የነበረውን አቋምን፣ አቦይ ስብሃት ሃቁን አቀያይረው ሲክዱ ስሰማ፣ ምናልባት ከዕድሜ የሚመጣ የመርሳት ችግር ካልሆነ?፣ እንደ ጭራ ለቀረችዋ ዕድሜያችን እንኳን ዋሽተን እውነቱንስ ተናግረን የሚበቃን ዕድሜ አለ ወይ ብዬ እራሴን ጠይቄያለሁ፡፡

ትዝብት ሁለት፣ እየመጣ ያለውን አደጋ ተገንዝበው፣ መፍትሄና አስታራቂ ሃሳብ ለማቅረብ እየሞከሩ የነበሩትን የአንዳንድ ተሳታፊዎችን አስተያየት ለማጣጣል፣ ብሔራዊ አደጋን በጋራ ስለመከላከል ብዙ ጊዜ ይነግሩን የነበሩትና፣ እራሳቸውን ወደ መሃል (ሞደሬት) ፖለቲካ እንደሚያዘምሙ ያመላክቱን የነበሩት ዶ/ር. መረራ ጉዲና፣ በብሔራዊ ችግራችን ዙርያ ያለውን አደጋን በጋራ መፍትሄው ላይ ከማተኮር ይልቅ፣ የቆሙበትን የብሔር ፖለቲካን የሙጥኝ ብለው ሲከላከሉ ተደምጠዋል፡፡ ባለፉት ጊዜያት በተደጋጋሚ በሚሰጡት ሃሳብና በሚያስተላልፉት ማስጠንቀቂያ፣ አሁን ያለው **ዘርንና ቋንቋን መሠረት ያደረገ የፌደራል ስርዓትን ዲሞክራታይዝ ማድረግ እንጂ መቀየር አያስፈልግም** ሲሉ፣ በዚህ ሥርዓት ምክንያት ሃያ ስምንት ዓመት ያሳለፍነው፣ አሁን በየቦታው እየደረሰ ያለው ችግርን ጨምሮ በቀጣዩ ምን ሊያስከትል እንደሚችል፣ እንዳላየና ምን? የባሰ ጉዳይ ይህንን ወደጎን ሊያስገፉ እንዳስገደዳቸው አልገባኝም፡፡

ዘርንና ቋንቋን መሠረት ያደረገን አክራሪ ብሔረተኝነትን ከዲሞክራሲ ጋር ማስተሳሰር ይቻላል ማለት፣ ፋሺዝም በዲሞክራሲ ማስተካከል ይቻላል ከሚለው ለይቼ ስለማላየው፣ ይህ ሊሆን የሚችልበትን መንገድ የፖለቲካ ባለሞያዎቹ በግልጽ ሊያስረዱን ይገባል፡፡ ይህ ማለት ግን ሁሉንም ዓይነት የፌደራል አስተዳደር አይጠቅመንም ማለቴ አይደለም፡፡

በተረፈ የውይይቱ የመጨረሻ ውጤት ለሀገር የሚጠቅም ፍሬያማ እንደሚሆን እየተመኘሁና ተስፋም እያደረኩኝ፣ ብዙ ነገር አንስቶ በመተቸት ወይም በመከራከር ጊዜዬን ከማባከን፣ በቀጥታ ለምናየው ችግራችን፣ ቀጥተኛ መፍትሄ በተራ ዜጋ ቀላል አገላለጽ ሃሳቤን ለማካፈል ልሞክር፡፡

በመጀመርያ በዘልማድ በተደጋጋም እንደሚነገረው፣ **"ሀገራችን ገና ውጤቱ በግልጽ ባለየለት በሁለት መስቀልያ መንገድ ላይ ነች"** የሚባለውን ምኞታዊና አዘናጊ አባባል ለጊዜው ትተን፣ በገሃድ እየተካሄደ ያለውን አደገኛ አዝማሚምያ፣ እየገባንበት ያለውን ማጥ፣ እየቀረበ ያለውን የባሰ ቀውስና የመበታተን አደጋ በድፍረት ሳንሸፋፍን እንዳለ መረዳትና መቀበል ግማሽ የመፍትሄ አካል ነው፡፡

**ምናልባት መስቀልና መንገድ ትርጉሙ ካልተቀየረ?** ለእኔ ያንን የአማራጭ መስመር አልፈነዋል፡፡ ከሦስት ሚልዮን ሕዝብ በላይ ከኖሩበት ስፍራና ለፍተው ከቋጠሩት ንበርታቸው ካለሕግ ተዘርፈውና ተሰቃይተው መፈናቀል፣ ባካባቢ የጸጥታ ሰዎች የታገዘ የደቦ ፍርድ ባደባብባይ ሲስተናገድ፣ ተምሮ ሥራ ለማግኘት ያልቻለው ወጣት በቡድን እየተደራጀ መንገድ ላይ መኪና እያስቆመና፣ ሀገር በቀል ድርጅቶችን የራሱን "ታክስ" ለማስከፈል የሚካሄደውን ሕገ-ወጥ ድርጊት እየሰማን፣ በየማኅበረ-ሰቡ ጥንፍ በረገጡ ጥቂት አክራሪ ብሔረተኛ አስተባባሪነት ለሚቀጥለው ግጭት የሚደለቀው የጦርነት ከበሮና እየደለበ ያለው ሰራዊት፣ በየከተማው የሚዘረፈው ባንክ፣ የጦርነት ፕሮፓጋንዳ፣ ሽለላውና ቀረርቶው፣ ስድቡና እንካ ሰላምታው.... አማራጭ መንገድ ላይ ቆሞ እያመነታ አይመስለኝም፡፡

አሊያ ከዚያ መስመር አለፈ የሚባለው ስንት? ሕዝብ ሲሞትና ሲፈናቀል እንደሆነ አሃዙን ነግረው ያስተምሩን፡፡ በተረፈ እንዳላወቀ ሆኖ ነገሮችን በምሁራዊ ቃላት ከመደባበስ፣ ችግር መኖሩን ተቀብሎ መፍትሄ ለመፈለግ መነሳት፣ ችግሩን እንኳን ሊያስወግድ ባይችል፣ እጅን አጣምሮ ምን አገባኝ ብሎ ከመቀመጥ ይሻላል፡፡ ከቦኋላ ጸጸትና ከጎሊና ወቀሳ ያድናል፡፡ ከዛም አልፎ ሙከራው ሊሠራ ይችላል፡፡ ምንም ነገር ተሞክሮ ከታየ ቦኋላ ነው መሥራት አለመስራቱ በእርግጠኝነት የሚታወቀው፡፡

በተረፈ በእንደዚህ አይነት ጠቃሚ ሀገራዊ ጉዳይ ላይ አስተያየት ለመስጠትም ሆነ ለማገዝ እንደሚከብድ ብረዳም፣ "ሰው ያለውን ከወረወረ ፈሪ አይባልም" እንደሚባለው፣ እንደ አንድ ተራ ሀገር ወዳድ ዜጋ ችግሩን እኔ እንዴት እንደማየውና የመሰለኝ መፍትሄውንም ለወገኖቼ ለማካፈል ስነሳ፣ ከኔ በጣም የላቀ ዕውቀት ያላቸውና በሙያውም ዘርፍ የዳበረ ተመክሮ ያካበቱ እንዳሉ ስለማምን፣ ምናልባት አወኩኝ ብዬ ከዘባረኩኝ፣ ምንጊዜም ከኔ ከተሻሉ ለመማር ፈቃደኛ መሆኔን ከወዲሁ ሳላሳውቅ አላልፍም፡፡ በተረፈ የሃሳብ ድግግሞሽን ለማስወገድ በሪፖርቱ ውስጥ ቀድሞ በሌሎች የተነሱትን አልደገግማቸውም፡፡

**<u>በውይይቱ እውቅና ያላገኙ ዓቢይ ችግሮቻችን፣</u>**

**ችግር 1- <u>አዲስ ወይም የተሻሻለ ሕገ መንግሥት</u>፣**-በጥቅሉ አሁን እየተሰራበት ያለው ሕገ-መንግሥት ሲዘጋጅ፣ ብዙ ጠቃሚ አንቀፆች ጭምር ቢኖሩበትም፣ "የሁሉንም ክፍል ሕዝባችንን ፍላጎት አላሳተፈም፣ ሊካተቱ የሚገባቸው ጠቃሚ ጉዳዮች አልተካተቱም" የሚል ቅሬታ በስፋት ስለሚሰማ፣ ይህንን ቅሬታ ለማስወገድ ባስቸኳይ የሁሉንም ውክልና ያካተተ አዲስ ወይም የሚሻሻል ሕገ መንግሥት ያስፈልጋል፡፡

ችግር 2- **<u>ዘርንና ቋንቋን መሠርት ያደረገ የፌደራል አስተዳደርን</u>፣ ሁሉም ወይም አብዛኛው ሊስማማበት በሚችል መንገድ የተዘጋጀ <u>የተሻለ የፌደራልም ሆነ ክፍለ ሀገራዊ</u>፣ ወይም ሁለቱን ያቀናጀ የአስተዳደር ሥርዓት እንዲተካ፡፡** ይህ ዘርንና ቋንቋን መሠረት ያደረገ የፌደራል አስተዳደር በሕዝባችን ውስጥ የአንድነትን መንፈስ አሳንሶ፣ አካባቢያዊ ውሱን ጥቅሙ ላይ ብቻ ተከልሎ እንዲያተኩር ከመገፈፋቱም በላይ፣ ለዘመናት አብሮ የኖረውን ዜጋ፣ ከሌላ አካባቢ በመምጣታቸውና፣ ምናልባትም የአካባቢውን ቋንቋ ባለመናገራቸው፣ እንደ አንድ ሀገር ዜጋ ሊያገኙ የሚገባውን መብታቸውን በማሳጣት እንደ ሁለተኛ ዜጋ ተቆጥረው በሰው ልጅ ላይ ሊፈጸም የማይገባው ግፍ ስቃይና መፈናቀል እየደረሰባቸው እንዳለ በገሃድ ታይቷል፡፡ ይህ ለሃያ ስምንት ዓመት በሕዝባችን ላይ የተሞከረው የቅኝ ገዢዎች አይነት አስተዳደር፣ ዜጎች በማንኛውም ስፍራ ተዘዋውረው፣ ንብረት አፍርተውና በችሎታቸው ሰርተው እንዳይበሉ መብታቸውን እንዳገደ ከብዙ በጥቂቱ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

**ችግር 3.- <u>አንቀጽ 8 በሕገ-መንግሥቱ የተደነገገው የቡድንን እንጂ የግለሠብን ነጻነትንና እንደ አንድ ዜጋ ኢትዮጵያዊ የመሆን መብትን ስለሚገድብ ይሻር፡፡</u> የዜጎች ልዑላዊነት መብት የሚጀምረው ከግለሰባዊ ነፃነት ተነስቶ፣ ስብስብ፣ ቡድን፣ ዕምነት..** እያለ ይቀጥላል እንጂ የተገላቢጦሽ ሊሆን አይገባውም፡፡ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ልዑላዊነት መከበር የሚገባው፣ የትም ቦታ ይኑር ምንም አይነት የፖለቲካ፣ እምነት፣ ባኅል ...ወዘተ ልዩነት ይኑረው፣ በቡድን ይደራጅ አይደራጅ፣ ኢትዮጵያዊ ሰው በመሆኑ ብቻ ነው፡፡ ምርጫ ስላልመረጠ፣ የፓርላማ አባል ስላልሆነ፣ ወይም በዘር ስላልተደራጀ፣ ልዑላዊነቱ ማጣት የለበትም፡፡ ስለዚህ የግለሰብም ይሁን የቡድንን መብትን መነጣጠል የልዑላዊነትን ትርጉም ሙሉ አያደርገውም፡፡ አንቀጹ ልዑላዊነት የሚያጎናጽፈው፣ በብሔር ብሔረ-ሰብ የተደራጁትን ብቻ ነው፡፡

**ችግር 4.- <u>ዘርንና ቋንቋን መሠረት ያደረገ የመልክዓ ምድር ካርታ ይወገድ</u>፣** በተግባር እንደሚታየው ሕዝባችን ለዘመናት በአንድ አካባቢ ብቻ ተገድቦ አልኖረም፡፡ በዘመቻ፣ በጦርነት፣ በሥራ፣ በድርቅ፣ በንግድና በጋብቻ....ወዘተ ምክንያቶች የሄደበት አካባቢ ተቀላቅሎና ተዋህዶ ነው የሚኖረው፡፡ በተለያዩ የአገዛዝ ሥርዓት የሕዝባችን አሰፋፈርና አኗኗር በተለያየ የታሪክ እርከን አንዳንዴ እየሰፋ፣ እየጠበበና ተዋህዶም እየተቀላቀሉ የሚቀያየሩትን መልክዓ ምድራዊ አከላለሎች፣ በየወቅቱ ለሥርዓቱ ቁንጮዎችም ሆነ ለአስተዳደሩ እንደሚያመቸው ተደርገው ነበር የተቀየሱት፡፡


በወያኔ የበላይነት ይታገዝ የነበረው አስተዳደርም፣ ለወያኔ በሚጠቅመው መንገድ፣ በጥናት ተነድፎ በተለያየ ቦታ ያካለላቸው፣ ይነጥቃቸውም ሆነ ያሸጋሸጋቸው የነበሩትም የተለየ ጥቅም ለገዢዎቹ እንዲጠብቅና፣ በተፈለገ ሰዓት እንደአሁኑ አይነቶች የክልል ግጭቶችን ለማነሳሳት፣ የመሬት ይገባኛል ጥያቄዎችን ፉክክር ለማስጦዝ፣ የዘር ማጥራት መፈናቀሎችን ለማነሳሳት እንዲያመች ተደርጎ **"እኛ ካልገዛናት እንበትናታለን"** ከሚል ስሌት ተነስተው በረቀቀ ጥናት እቅድ እንደተሰራ አሁን በተግባር እያየነው ነው፡፡

ይህ በየቦታው የመፈናቀል አደጋ ተከስቶ ያስከተለው ችግር፣ በሕዝባችን ውስጥ የበለጠ ፍርሃትና በቀጣይ ምን ሊፈጠር እንደሚችል እርግጠኛ አለመሆንን ስለሆነ፣ በምናልባት ከሚከተለው አደጋ እራስን ለመከላከል በሚል፣ ለሚቀጥለው የማያባራ እልቂትና ስደት የተጧጧፈ ዝግጅት እንደሚደረግ የማያስተውል፣ አውቆ የተኛ ወይም በምኞት መኖር የሚሻ ብቻ ነው፡፡ በሕጋዊ መንገድ ለመለያየት የተመቻቹትን ሕገ-መንግሥታዊ አንቀፆችን ሳይዘነጉ፣ ከዚህ አይነት የእርስ በእርስ ግጭቶችና ትርምሶች ቦኋላ አብሮ ለመቀጠል ምን ያህል አስቸጋሪ ሊሆን እንደሚችልና፣ ከትርምሱ ቦኋላ አስቀምጦ የሚያልፈው የታሪክ ጠባሳ በቀላሉ እንደማይጠፋ ከሌሎች ሀገር ጥፋት መማር ይኖርብናል፡፡

ይህንንና መሰል አደጋዎች ለማስወገድ በአንዳንድ አርቀ አስተዋዮች ካሁን በፊት እንደተጠቆመው፣ ከዘርና ቋንቋ አከላለልም በተሻለ፣ **"ሰሜን፣ ደቡብ፣ ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ እና መካከለኛ ኢትዮጵያ"** በሚል ቢደራጅ፣ **ጥንፍ የረገጠ አካባቢያዊና የአሃዳዊ ስሜትን** በሂደት አስወግዶ፣ በአብሮነት ላይ የተመሠረተ መንፈስ ያሳድጋል፡፡ ሁሉም ቦታ በጋራ፣ ሁሉም ማኅበረሰብ ስለሚኖር አካባቢያዊ ስሜትን ያሰክናል፡፡

ይህ እያንዳንዱ ማኅበረሰብ እንደፍላጎቱ የራሱን ባኅልና ቋንቋ የመጠቀም ነጻነትን ካለመገደቡም በላይ፣ በሂደት ክልላዊ ስሜቶች እየቀነሱ መቀራረብ ሲጀመር፣ ሰዉ ብቻ ሳይሆን ቋንቋውና ባህሉም ጭምር አንዱ ከሌላው እየተዋዋሰና እየተዋሃደ የሀገር ግንባታውን ጭምር ሳይደናቀፍ ይበልጥ የሚያፋጥነው ይመስለኛ፡፡

ይህ አይነት አካሄድ ምናልባት በቀውሳችን ሊያተርፉ ወይም ወድቀታችንን ለሚመኙልን የውጪም ሆነ የውስጥ ጠላቶቻችንና፣ አክራሪው ብሔረተኛ ምሁሮችን፣ በመሬት ይገባናል ጥያቄ ስም እንደፈለጉ በየጊዜው አዳዲስ የክልል ማፕ በወረቀት እያጠሩ፣ ሕዝባችንን ከፋፍለውና አንዱን በሌላው ላይ አነሳስተው፣ ለመሬት ሽሚያ በሕዝብ ሕይወት ስልጣን ለመጨበጥ ከሚጥሩት በስተቀር፣ ማንንም ለሀገሩ በጎ ነገር ለሚመኝ ሊያስከፋው የሚችል አይመስለኝም፡፡ **ለምሳሌ ያህል** ከዚህ በታች የምትመለከቱት ሊሻሻል የሚችል እንደ አማራጭ ሆኖ የቀረበ፣ በአምስት ክፍለሀገራት ለማቀናበር የተሞከረ የመልካዓ-ምድር ካርታ ተቀባይነት ቢያገኝ፣ ብዙ ወደፊት ሊገጥሙን ከሚችሉ ችግሮች ያስወግድልን ይሆናል፡፡




ይህ አማራጭ እንደ መንደርደርያ ምሳሌ ለማሳየት እንጂ፣ ተፈጥሮዋዊ የወንዞቹንና የተራሮቹ ወጣ ገባ አቀማመጡ በተግባር ምን ሊያስቸግር እንደሚችል ለካርታ ባለሙያዎች ትተን፣ ቁጥሩ ግን በአሳማኝ ምክንያት ሊያንስ ወይም ሊበዛ አሊያም የተለያየ አማራጭ ማቅረብ ይቻላል፡፡ ምናልባት ለዘመናት ያቺ እያየናት ከኛ ጋር ተዋኅዳ የኖረችውን ካርታ መርሳት አስቸጋሪ እንደሚሆን ግልጽ ነው፡፡

ዋናው ቁም ነገሩ <u>ሁሉም ሕዝብና መሬት የኛ ነው! እኛም የሁሉም ነን!</u> የሚለውን አስተሳሰብ፣ ካሮጌው "ለእኔ" ወይም "ለእኛ ብቻ" ከሚለው ለማላቀቅ ይረዳል ከሚል ሃሳብ በመነሳት ነው፡፡ ጥቂቶች አካባቢያዊ አስተሳሰብ በውስጣቸው አደልበውና፣ ስር በሰደደ ጥላቻ ተጠቅጥቀው፣ ጤነኛ ባልሆነ የፉክክር ስሜት ለብዙ ጊዜያት በአሉታዊ ምኞት ኅሊናቸውን ስላሳመኑ ይህ አይነት አደረጃጀት የያዙትንና ገና ወደፊት የሚያልሙትን ጥቅምና ሥልጣን የሚያሳጣቸው መስሎ ሊያስፈራቸው ይችላል፡፡

የአንድ ሀገር ካርታ ቀርቶ የተቀደሱ የዕምነት ማጻህፍትን እንኳን ከጊዜው ጋር ለማራመድ፣ ሊቃውንቱ ቁጭ ብለው ተመካክረው እየከለሱ ያሻሽሏቸዋል፡፡ የሕዝብን ችግርን ለማስወገድ፣ ሕዝብ ከተስማማበት! ተሻለ አማራጭ አቅርቦ መቀየር ማስተካከልና መለወጥ እንደታቦት ሊነካ መፈራት የለበትም፡፡ ዛሬ መንግሥት እንዳላየ ሆኖ እያለፋቸው ያሉ ቅጥ ያጡ፣ <u>ወሰን፣ ድንበር፣ ካርታ፣ ባንዲራን</u> ጨምሮ የተዘበራረቀ አሰራርን በአስቸኳይ በሕግ ስርዓት ማስያዝ፣ ወደፊት በነዚህ ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ ግጭቶችን ማስወገድ መሆኑን መረሳት የለበትም፡፡ የእስፖርት፣ የፋብሪካ፣ የክለብ፣ የፖለቲካ ስብስብ..... ወዘተ ባንዲራ በቦታው መስቀል ነውር የለውም፡፡ ሆኖም የተባበሩት መንግሥታትን ቢሮ እስከምንመስል፣

የውጪ ዜጋዎችን፣ ብሔራዊ ባንዲራን አስወግደን በሰፈር ባንዲራ ማስተናገድ፣ የቱ መቼ መሆን እንዳለበት መንግሥት ግልጽ መመርያ አለማውጣትና ዝም ብሎ ትርምሱን ማየት ግራ ያጋባል፡፡

ወደ ሕዝብ ውስጥ ዘልቀው ገና ባይገቡም፣ በተለያየ ጽንፍ በቆሙ አክራሪ አስተሳሰቦች ዳብረውና በደቦ ተከታዮችም ጭምር ታጅበው የምናየውን ሃቅ፣ ቀርበን ሁኔታውን ባስቸኳይ ለመለወጥ ካልቻልን፣ ችግሩን ለፌስቡኮችና ለማኅበራዊ መገናኛ አክቲቪስቶች ትተን ቤታችን ብንቀመጥ፣ ይህ ስሜት እየጦዘ ወደ ሕዝብ ተገፍቶ ተቀባይነት ካገኘ ቡኋላ ማስቆም ከባድ ነው፡፡ ችግሩ ስር ሰዶ ከዚህ የባሰ ሁኔታ ውስጥ እንድንገባ ብዙ ምክንያቶች ያላቸው በትጋት የሚንቀሳቀሱ እንዳሉ መዘንጋት አያስፈልግም፡፡ እነዚህ ክፍሎች የሚፈልጉትን ለማስፈጸም፣ በቂ ገንዘብ፣ ድርጅት፣ በተንኮል የዳበረ ልምድ፣ ሰፊ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ኔት ወርክ ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ፣ ለነዚህ ክፍሎች ግልጋሎት ሊሰጡ የሚችሉ፣ ከየማኅበረሰቡ በግላዊ ቁስል ሕዝባችን ላይ ያቄሙ፣ በመጥፎ ሱሶች የደከሙትን ለሚፈልጉት ተግባር በየጉራንጉሩ እንደሚገለገሉባቸው መዘንጋት አያስፈልግም፡፡

አክራሪ ብሔረተኞች የሕዝብን ስሜት ሊያነሳሳ የሚችል ነገር ፈልገው እየኮረኮሩ ሕዝባችንን እርስ በእርስ በማጋጨት፣ በሕዝብ ተወካይነት ሽፋን ወደ ሥልጣን ለመንጠላጠል የሚፈልጉት በሁሉም ማኅበረ-ሰብ ውስጥ ያሉት ጥንፈኛ ምሁራንን ሥራ ፈት ለማድረግ ከላይ የተጠቀሰው አዲስ አይነት አካሄድ ከመጀመር የተሻለ አማራጭ መኖሩን እጠራጠራለሁ፡፡ በዚህ አይነት ከሚገኘው ሠላም፣ መረጋጋትና እድገት ተጠቃሚ የሚሆነው መላው ሕዝባችን መሆኑን መጠርጠር የለብንም፡፡ በቅንነት ነገሮችን ሰፋ ተደርጎ ሀገርን ከጥፋት ለማዳን ከታሰበ፣ ከጽንፈኞች መለስ በብሔር ዙርያ የተደራጀቱንም ሆነ በአንድነት ዙርያ ያሉት፣ ወደ እዚህ አይነት የአብሮነት አካሄድ እራሳቸውን ቢያስተካክሉ ሕዝባችንን ሊመጡ ከሚችሉ አደጋዎች አድነዋት ገንቢ ታሪክ ለሀገራቸው ይሰራሉ፡፡ እስካሁን ባልተሞከረ አዲስ አካሄድ አስበውና የጋራ አጀንዳ ቀርጸው፣ ሀገርን ለመገንባትና የሕዝባችንን ሕይወት ወደተሻለ ደረጃ ከፍ ለማድረግ የሚያስማማቸው ብዙ ብዙ ምክንያቶች አሏቸው፡፡

**ችግር 5.- አንቀጽ40. <u>መሬት ላራሹ!</u> ካለ የቃላት ጨዋታ በሥራ ይተርጎም!** በእርግጥ ይህ ርዕስ በውይይቱ ውስጥ የተነሳ ቢሆንም፣ **"የባለቤትነትና ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን በሚያረጋግጥ መልኩ ቢሻሻል"** ተብሎ በአሻሚ ቋንቋ ተድበስብሶ የታለፈ ይመስላል፡፡ ይህ ወደ ሃምሳ ዓመታት ትውልዱ አንስቶ እየታገለ ዋጋ የከፈለለትን ጥያቄ፣ ደርግም ሆነ በወያኔ አስተዳደር፣ መሬትን ለፖለቲካ መሳርያነት ለመጠቀም በነበራቸውስሌት፣ መንግሥት መሬቱን በአፈላማ ይዘው ከላይ የተጠቀሰው አይነት የተለያየ ሕጋዊ መሰል በተሸፋፈነ ቃላት ይጫወቱ እንጂ፣ የመሬት ላራሹ መልስ እስካሁን አልተመለሰም፡፡

ባለቤት ማለት ሕግ የሚጠይቀውን ደንብና ክፍያ እስካሟላ ድረስ፣ ንብረትን መሸጥ፣ መለወጥ፣ ወለድ አገድ ማስያዝ. የማውረስ፣ የመሸለምና የማስተላለፍ....ወዘተ መብትን በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ ከወቅቱ ጋር ለመራመድ የአስተሳሰባችን መንገድ ካልተቀየረ፣ የፈለገ ምርጫና የአዋጅ ጋጋታ ቢተላለፍ፣ ዲሞክራሲን በሕዝብ ላይ በሃይል ማስፈን አይቻልም፡፡ መጀመርያ የማይጠቅመንን ኋላ ቀር አስተሳሰብ ትተን አዕምሮዋችንን ለለውጥ ካላዘጋጀን፣ ዲሞክራሲን ጠቅልለው ቢያጎርሱን፣ "መላዕክት ከሰማይ ወርደው ቢያስተዳድሩን" ምንም አያረካንም፡፡ ምክንያቱም ከዘረኛና ከጠባብ ድርጅታዊ ፍቅር እራሳችንን ስላላላቀቅን፣ ነገሮችን የምንመዝነው ከዘርና ቅጥ ካጣ ጭፍን ድርጅታዊ ፍቅር በስሜት ብቻ ተነሳስተን ስለሚሆንና ከነባራዊ ሁኔታ ስለሚያርቀን፣ ይህም አካሄድ ጥንፍ ከረገጠ ደጋፊነትም ይሁን ተቃዋሚነት ጎራ ተሰልፎ የወገናችንን ስቃይ ከማራዘም ተግባር አያድነንም፡፡ ስለዚህ ምርጫችን ለከፊሉ ሳይሆን ለመላው ሕዝባችን፣ ሠላም፣ ኅብረትና ብልጽግናን ለዘለቄታው ሊያመጣልን ከሚችል ጠካራ ፍላጎትና በጋራ ከተቀናጀ መንፈስ በመነሳት፣ የተጀመረውም የለውጥ ሂደት አቅጣጫው እንዳይቀየርም ሆነ እንደተለመደው <u>እንደገና እንዳያመልጠን</u> ሁሉም የድርሻውን ሃላፊነት ለመወጣት ቢጥር፣ ላቅ ወዳለ ደረጃ ተራምደን የተሻለ ለውጥ እናመጣለን ብዬ እንደ አንድ ሀገር ወዳድ አምናለሁ፡፡

ኢትዮጵያ በልጆቿ ኅብረት ትድን ዘንድ እግዚአብሔርም ይርዳን! tebaber@gmail.com